


# አባ ይሁዳ

አባ ገ/መድህን ፣ አባ ገ/ይሁዳ
ሃይማኖት የሌለው ፣ ማተቡን የከዳ
ለስጋው ያደረ ፣ የተልከሰከሰ
ህግጋትን ሽሮ ፣ ወጉን ያፈረሰ ።

የቤተ ክህነቱ ፣ ቢልጭሊጭ ቅምጥል
በደረቱ ሙሉ ፣ ወርቅ የሚያንጠለጥል
ቤተ እግዚሃር ፣ ገብቶ ሰው የሚዘነጥል
የሚባርክ  መስሎ ፣ በጥይት የሚጥል ።

መኳኳል የሚወድ ፤ በሽቶ ተነክሮ
ሁሌ ነጭ ለባሽ ፣ ሁሌ ተሞሽሮ
በበጎች መሃከል ፣ የገባ ቀበሮ
ስርአት አፈረሰ ፤ ለዲያቢሎስ አድሮ ።

ካድሬ ይሁን ካህን ፣ ውሉ ያልታወቀ
እንደ ድንግሎቹ ፣ ቀሚስ ያጠለቀ
ሽጉጥና መስቀል ፣ አብሮ የታጠቀ
በደም በሙስና  ፣ የተጨማለቀ ።

ሺ ዓመት ተጠብቆ ፤ የነበረን ስርዓት
ጳውሎስ የዮዲት ልጅ ፤ ንዶ አፈራረሳት
በቤተ ክህነቷ ፤ ሰደደባት እሳት ።

ታዛቢው

August 28/2009